# አስቸኳይ ተግባራዊ ጥሪ (CLARION CALL) ለኢትዮጵያውያን በሙሉ

## በተለይም ለኦሮሞ ወገኖቼ

ከይኄይስ እውነቱ

የትግሬ ወያኔ (ሕወሐት )እና በመልኩና በአምሳሉ የፈጠራቸው የየጎሣው ‹‹ወያኔዎች›› መረን ወጥተው በዚህ ታላቅ ሕዝብና በዚህች ታላቅ አገር ገና ከማለዳው የጀመሩትን ግፍና በደል ዝም ብለን ተሸክመን መቆየታችን ዛሬ አገሪቱንና ሕዝቡን ሊያጠፉ ወደተቃረበ የግፍና ጭካኔ ማዕበል ላይ አድርሶናል፡፡ ግንዱ ወያኔ ሲገረሰስ ቅርንጫፍ የሆኑት ተላላኪ አሽከሮችም ድራሻቸው እንደሚጠፋ ጥርጥር ባይኖርም በአሁኑ ሰዓት ማንነቱ ፍንትው ብሎ ከታወቀውና መነሻውም መድረሻውም አገርንና ሕዝብን ማጥፋት ከሆነው ሕወሐት ይልቅ ሕዝባችንን ለእልቂት አጋልጠው የሰጡት በየመንደራችን ያሉት ግልገል/ቅጥረኛ የሕወሐት ባሪያዎች ናቸው፡፡ በቢሾፍቱ ከተማ በወገኖቻችን ላይ የደረሰው አሳዛኝና አሰቃቂ እልቂትም ዋነኛ ተዋናዮች የተላላኪው ኦሕዴድ ካድሬዎች ናቸው፡፡ የእነዚህ ሆድ አምላኪዎች ወሳኝ እገዛ ባይኖር ወያኔ በሁሉም የአገሪቱ ማዕዘናት አሁን እየወሰደ ያለውን በእብሪትና በንቀት የተሞላ ጭፍጨፋ እውን ማድረግ ባልቻለ ነበር፡፡ በጎንደርና በባሕር ዳር፣ በኮንሶ፣ በጋምቤላ፣ በአፋርና በኢትዮጵያውያን ሶማሌ፣ በሌሎችም የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገራት ውስጥ ወያኔ እንደ ልቡ የሚፈነጨው ታማኝ አሽከሮቹን (ብአዴን፣ ኦሕዴድ፣ ደሕዴድ እና አጋር ተብዬዎች) ተማምኖ ነው፡፡ ከነዚህም መካከል አንዳንዶቹ በጎሣ እውነተኞቹ ወያኔዎች መሆናቸው የአደባባይ ምሥጢር ነው፡፡ እነዚህ ድውያን አገልጋዮች የሚያስቡበት የራሳቸው አእምሮ፣ የሚያስተውሉበት የራሳቸው ልብ፣ የሚያዩበት የራሳቸው ዓይን፣ የሚሰሙበት የራሳቸው ዦሮ የላቸውም፡፡ ይህንን ኹሉ የሚፈጽምላቸው ‹ፈጣሪያቸው› ሕወሐት ነው፡፡ ያሬድ ጥበቡ የተባለና ለወያኔ በማደር የማለዳ ሰለባ የሆነ ሰው ለነዚህ ጭንጋፍ (ሞተው ለተወለዱ) ጥብቅና ሲቆም (አቋሙንና ዓላማውን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ ያደረገ ይመስለኛል) ጊዜው የእሰጣ ገባ አይደለም በሚል ብዙዎቻችን ንቀን አልፈነዋል (ብዙ ማለት ቢቻልም)፡፡ ከእነዚህ ‹ቅጥረኞች› መካከል በአጋጣሚ ማስተዋልን ገንዘቡ ያደረገ ከተገኘና አሰላለፉን ከሕዝብ ጋር ካደረገ ተበዳዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርታውን አይነፍገውም፡፡

ወደቀደመ ነገሬ ልመለስና ኦሮሞው ኢትዮጵያዊ ወገኔ ከእንግዲህ ወዲህ ያንተ ግምባርና ደረት በአጋአዚ ጥይት ሲመታ ማየትም መስማትም አልፈልግም፡፡ እንደ ጎንደርና ጎጃም ወገንህ ራስህን በሚገባ ተከላከል፡፡ ከዋናው ወያኔ ጋር ከመፋለምህ በፊት በአካባቢህ ያለውን ቅጥረኛ የኦሕዴድ ካድሬ (በጎሣ/በቋንቋ አንተን መስሎ የሚያስገድልህን) መንጥረህ ለይና ተፋለመው፡፡

ግንዱን ወያኔ ካንተ ጋር ሆኖ ለመፋለም ፈቃደኛ የሆነውን ከጥንቃቄ ጋር እጅህን ዘርግተህ ተቀበለው፡፡ በዚህ ረገድ ለሚደረገው ትግል ከልሂቅ እስከ ደቂቅ አገር ውስጥ ያለንም ሆነ ውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ሁለገብ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

ቅርንጫፎቹን በሚገባ ከመለመልን ግንዱን ወያኔ (ሕወሐት) ዕርቃኑን እናስቀረዋለን፡፡ ለኢትዮጵያውያን አሁንም ጊዜው ‹ክረምት› ነው፡፡ የተዘራው የነፃነት አዝመራ አብቦ አፍርቶ

መልካም ፍሬ እንዲሰጥ ከፈለግን አረማሞውን ነቅለን ማስወገድ የግድ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ዘመን መለወጫ/እንቁጣጣሽን፣ ታላቁን የምሥጋና በዓል እሬቻን በአንድነት ሆነን በነፃነትና ሰላም እናከብራለን፡፡

ይህ አስቸኳይ ተግባራዊ ጥሪ በተመሳሳይ መልኩ ኢትዮጵያውያንን በሙሉ ይመለከታል፡፡ ለነፃነታችን የማሰናከያ ደንጊያ/እንቅፋት የሚያኖሩትን ወያኔን እና ባጠገባችን የሚገኙትን ታማኝ አሽከሮቹን ለይተን እንፋለማቸው፡፡ ቅድሚያ ለኋለኞቹ ሰጥተን፡፡ ገባሮቹን ስናደርቅ ዐባይ የሆነው ወንዝ ይነጥፋል፡፡ ለወያኔ ሥልጣንና ዝርፊያ መሠረቶቹ ገባሮቹ መሆኑን አንዘንጋ፡፡

***ለጽዮን ልጆች በድጋሚ፤*** ትግሬው ሕወሐት ከቅጥረኛ አሽከሮቹ ጋር እየፈጸም ያለውን እልቂት እናንተም ምስክሮች ናችሁ፡፡ እናንተ ጋር ቅጥረኛ ቅርንጫፎች የሉም፡፡ አለመታደል ሆኖ ያላችሁበት የኢትዮጵያ ክፍል የግንዱ ወያኔ መብቀያ/መሠረት በመሆኑ ከቀረው ወገናችሁ ጋር በመተባበር እዚህ መርዛማ ግንድ ላይ *ምሳራችሁን* በተግባር የምታሳርፉበት ጊዜ አሁን ነው፡፡

***‹‹ለአገር መከላከያ ሠራዊት›› በድጋሚ፤***ለወያኔ የግፍ ተግባር ተባባሪ በመሆን ከወገናችሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ከዕለት ወደ ዕለት እየራቃችሁ የባዕድ ጦር የሚያስመስል ተግባር ውስጥ እየገባችሁ መሆኑ ሕዝባችንን አስቆጥቷል፣ አሳዝኗል፡፡ ይህ እስከ መቼ ነው የሚቀጥለው? በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች በሕዝብ ላይ የሚደርስ እልቂት በአጋአዚ ጦር ብቻ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ቢያንስ ወገናችን ላይ ጥይት አንተኩስም ማለት እንዴት አቃታችሁ? አሰላለፋችሁን ከወዲሁ ማሳመር አለባችሁ፡፡ ዋስትና የሚሰጣችሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጂ መቀበሪያውን እያፋጠነ ያለው ወያኔ አይደለም፡፡

***በሁሉም የእምነት ተቋማት ውስጥ ለምትገኙ እውነተኛ የሃይማኖት አባቶች በድጋሚ፤*** በሁሉም የእምነት ተቋማት ውስጥ የወያኔ ረጅም እጅ እንዳለ ቢታወቅም ፍርድ ሲጓደል ደሀ ሲበደል በፍርሃት ተሸብባችሁ ዝምታን እንዴት መረጣችሁ? በቅንነት ልታገለግሉት ቃል የገባችሁለት አምላክ እንደዚህ ዓለም ገዢዎች በጊዜ በቦታ የማይወሰን፣ በድካም በሞት የማይለወጥ የገዘፈ ኃያል አይደለም እንዴ? የፍጡሩ ደም በከንቱ ሲፈስ የእናንተ የእንደራሴዎች ኃላፊነት ምንድን ነው? ቢያንስ ለሞቱት ወገኖቻችን በይፋ ጸሎት ማድረግ አይገባም? የሟች ቤተሰቦችን ማን ያጽናናቸው? ዛሬ ያላገለገላችሁትና ጠባቂ ያጣ ምእመን ነገ እንዴት ቃላችሁን ሰምቶ ይታዘዛል?

በመጨረሻም የአንድም ኢትዮጵያዊ ንጹሕ ደም በከንቱ ፈሶ አይቀርም፡፡ ደም ሲያፈስ የኖረውም በሕይወት ከቆየ እንደባነነ፣ እንደደነበረና እንደተቅበዘበዘ ይኖራል፡፡

ልዑል አምላክ የኅብረትና የአንድነት መንፈሱን አሳድሮብን የሕዝባችንን ነፃነት ያቅርብልን፡፡ በኢትዮጵያ ላይ የተነሱ አዋልደ ዲያቢሎስን ዕድሜ ያሳጥርልን፡፡ በግፍ ያለቁ ወገኖቻችንን ነፍስ እግዚአብሔር ይማርልን፡፡ ለቤተሰቦቻቸውም አጽናኝ መንፈሱን ይላክልን፡፡